የተከበራችሁ የ ACPS ሰራተኞች፣ ቤተሰቦችና ማህበረሰብ፣

ከዩናይትድ ስቴትስ የበሽታዎች መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል (CDC) በተሰጠው ይፋዊ አስተያየትና ኮሮና ቫይረስ በማህበረሰባችን ላይ የሚያሳድረው ጫና አሳሳቢ እየሆነ በመምጣቱ ምክንያት፣ ACPS ኮሮና ቫይረስን (COVID-19) በተመለከተ ስላዘጋጀው ዕቅድ የሚከተሉትን መረጃዎች ልናጋራችሁ ፈልገናል። CDC የትምህርት ቤት ሃላፊዎች ሊከሰት ለሚችለው ወረርሽኝ እንዲዘጋጁ እየጠየቀ ነው። በዚህ ሰዓት፣ በአሌክሳንድሪያ፣ ቨርጂኒያ ውስጥም ሆነ በዲሲ አካባቢ በበሽታው መያዙ የተረጋገጠ ሰው የለም። በአካባቢያችን ውስጥ በ COVID-19 መያዙ የተረጋገጠ ሰው ድንገት የሚገኝ ከሆነ በሚል ACPS ከአካባቢና የክልል ጤና ሃላፊዎች ጋር በቅርበት እየሰራ ነው።

ACPS ከአሌክሳንደሪያ ከተማ የጤና መምሪያ እና ከአከባቢው የአድንገተኛ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በጋራ በመሆን የ COVID-19 ግብረ ሃይል ዕቅድ ዝግጅት ኮሚቴ ያዋቀረ ሲሆን፣ ይህም በየጊዜው እየተለዋወጠ ያለውን ሁኔታ በቅርበት ለመከታተል የሚያስችል ነው። በዚህ የዕቅድ ዝግጅትና ስራ የተወሰነ እርምጃ ስንራመድ የደረስንበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማሳወቅ አቅደናል።

የአሌክሳንደሪያ የጤና መምሪያ አሁን ያለውን የኢንፍሉዌንዛ ምላሽ አሰጣጥ ዕቅድ እየከለሰ ሲሆን፣ ለ COVID-19 ክስተቶች ምላሽ ለመስጠት ማናቸውንም አስፈላጊ ማሻሻያዎች እያደረገ ነው። ACPS የድንገተኛ አገልግሎት ዕቅዶቹን እየገመገመ ሲሆን፣ ስለ COVID-19 ተጨማሪ መረጃ ሲገኝ ዕቅዶቹ የሚከለሱ ይሆናሉ።

የ COVID-19 ሙሉ ተጽእኖ ግልጽ ባለመሆኑ ምክንያት፣ ACPS እና የከተማችን አጋሮች ለማንኛውም ክስተት እየተዘጋጁ ናቸው። በአሁኑ ሰዓት፣ የፌዴራል የጤና ሃላፊዎች ትምህርት ቤቶች ትምህርት እንዲያቆሙ ምክር ሃሳብ አልሰጡም። የ ACPS የትምህርት ቤት ጤና አገልግሎቶች ትምህርት ቤቶች በተለይም ተማሪዎች ከቫይረሱ ጋር የተያያዙ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ወቅት የተማሪዎችን ሰውነት በተመለከተ በንቃት እንዲከታተሉ ለማድረግ እየሰራ ነው።

እንደ ማስታወሻ፣ የጉንፋን እና የኢንፍሉዌንዛ ቫይረሶች በክረምት ወቅት የተለመዱ ናቸው። ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ይመከራል። ሁሉም ሰው ጤናውን ለመጠበቅ የራሱን ድርሻ እንዲወጣ እንጠይቃለን። እባካችሁ እጃችሁን በተደጋጋሚ ታጠቡ፣ ጤናችሁን ተከታተሉ፣ ተማሪዎቻች የጉንፋንና የኢንፍሉዌንዛ ዓይነት ምልክቶችን ሲያሳዩ ከቤት እንዳይወጡ አድርጉ።

ስለ COVID-19 ተጨማሪ መረጃ ከአሌክሳንደሪያ ጤና መምሪያ፣ ከቨርጂኒያ ጤና መምሪያና ከዩናይትድ ስቴትስ የበሽታዎች መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል ማግኘት ይቻላል።

The Alexandria Health Department
Virginia Health Department
Centers for Disease Control and Prevention

ለድጋፋችሁ እናመሰግናለን። በዚህ ሒደት ውስጥ የሚከሰቱ አዳዲስ ነገሮችን እናሳውቃለን።

ከልባዊ ሰላምታ ጋር፣

Dr. Gregory C. Hutchings, Jr.
የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ